OPC-DC
Office of the People's Counsel
ADVOCACY | EDUCATION | PROTECTION

**የተጠቃሚ መማክርት**
**ሴፕቴምቤር 5 ቀን 2023**

# እንደ Verizon ሽግግሮች የአከባቢ የስልክ አገልግሎት መሳሪያ የአገልግሎት መቋረጥን ያስወግዱ

ከወደኋላ ከጃንዋሪ 2023 ጀምሮ፣ አንዳንድ የ Verizon ተጠቃሚዎች ድርጅቱ በኮፐር ሽቦ መስመሮች የስልክ አገልግሎቶችን ከዚህ በኋላ እንደማይሰጥ ተነግሯቸዋል። ከ Verizon ጋር የአከባቢውን የስልክ አገልግሎትን ለማስቀጠል፣ ከአከባቢው ኔትዎርክ ጋር ለማገናኘት ጥቅም ላይ የሚውለውን የመሳሪያ ዓይነትን ለመለወጥ Verizon ቤታቸው ላይ ወይም የንግድ ቦታቸው ላይ የመስራት ዕድልን ሊሰጡት ይገባቸዋል። አዲሱ መሳሪያን ለመግጠም "የገመድ/ፋይበር-ኦፕቲክ" የተባለውን የኤሌክትሮኒክ መገናኛዎችን ይጠቀማል። ይህም ተጠቃሚዎች "FiOs," መምረጥ አለባቸው ማለት አይደለም፤ የኮፐር ሽቦዎችን ከመቀጠል ይልቅ፣ የአከባቢያቸው የስልክ አገልግሎት ብቻ በዲጂታል ከስልክ ሥርዓቱ ጋር ይያያዛል።

**ማድረግ ካልፈለኩስ?**

እንደ **Verizon** ከሆነ፣ በካምፓኒው ዌብሳይት ላይ እንደተለጠፈው፣ ለ Verizon ሙብት የማይሰጡ ወይም ግንኙነት ያላደረጉ ተጠቃሚዎች አገልግሎታቸው ለጊዜው ይቆምባቸው እና ቀስ በቀስም ይቋረጥባቸዋል።

> የእርስዎ Verizon *አገልግሎቶች ለ Verizon ወደ እርስዎ ተቋማት ለመዘርጋት፣ ለመጠገን፣ ወይም መሳሪያዎቹን ለመለወጥ እና መሰረተ ልማቶቹን ማለትም እርስዎ የሚያገኙትን አገልግሎት ወደ ሽቦ/ ፋይበር-ኦፕቲክ መሰረተ ልማቶችን ለማዞር የሚያስችለንን ተገቢ የሆነ ፈቃድ ካልሰጡ አገልግሎቶችን ለጊዜው ይቆማል።* እንደ የእርስዎ አገልግሎት ለጊዜው ከቆመ፣ ወደ 9-1-1 እና ውደ ተጠቃሚ አገልግሎት ቁጥር ማለት ወደ 1.800.VERIZON (1.800.837.4966) ብቻ መደወል ይችላሉ። በግምት *14 ቀናት ያህል ለጊዜው ከቆመ በኋላ፣ የ Verizon አገልግሎት ከእርስዎ አድራሻ ላይ* እርስዎ ወደ አዲሱ ሽቦ/ፋይበር-ኦፕቲክ መሰረተ ልማቶች የእርስዎን አገልግሎት እንድናዞር ፈቃድ ካልሰጡን በስተቀር ይቋረጣል።" https://www.verizon.com/home/fiberupgrade/

**ይህ ለምን ይሆናል?**

የሆነ ጊዜ፣ የኮፐር ሽቦዎች በዩናይትድ ስቴት ውስጥ ለድምጽ እና ለኢንተርኔት ግንኙነቶች የጀርባ አጥንት ሆነው አገልግሎት ሰጥተዋል። ሆኖም ግን ባለፉት ጥቂት ዓመታት፣ ትልቁ የስልክ አገልግሎት አቅራቢ የተለመዱትን አሮጌ የስልክ አገልግሎትን በአዲሱ የሽቦ መሰረተ ልማት አገልግሎትን ኢንተርኔትን-መሰረት ያደረጉ የፋይበር ኦፕቲክ

ሽቦዎችን በኩል ለመስጠት በከፍተኛ ደረጃ እየቀየራቸው ይገኛል። እንደ አቅራቢዎቹ፣ ለተለመደው የመስመር አገልግሎት የሚደረገው ድጋፍ እየቀነሰ የመጣ ሲሆን አዲሱ የፋይበር ኦፕቲክ መሰረተ ልማት ግን ይበልጥ አስተማማኝ፣ ለጥገናም ዋጋው ርካሽ፣ እና ካለፈው ከአሮጌው የስልክ አገልግሎት ሰጭ ሽቦ ይልቅ የበለጠ መረጃን ለማስተላለፍ የሚያስችል ነው።

**ይህ ለተጠቃሚዎች ምን ማለት ነው?**

እንደ Verizon እምነት፣ እነዚህ ሕጋዊ የሆኑ የድምጽ አገልግሎቶች ከኮፐር ሽቦ ወደ ፋይበር ይዛወኣሉ ማለት ነው። Verizon መስራት የሚያቆም እና እንዲሁም የእርሱን የኮፐር ሽቦ መሰረተ ልማትን ሊያስወግድ ይችላል። ወደ ፋይበር ሽቦ ማዘዋወሩ ተጠቃሚዎቹ ላይ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ወጪ ሳያስወጣ ይደረጋል። የስልክ አገልግሎት ተመሳሳይ ዋጋን፣ ስምምነቶችን እና ቅድመ ሁኔታዎች የሚይዝ ይሆናል። የ Verizon ከፍተኛ ፍጥነት ያለው የኢንተርኔት አገልግሎትን በኮፐር ሽቦ ለማግኘት ይከፍሉ የነበሩ ተጠቃሚዎች ፋይበርን- መሰረት ያደረገ ሽቦ ምርትን በመምረጥ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎትን ከሌላ አቅራቢ ማግኘት ይችላሉ።

አብዛኛው ተጠቃሚዎች የኮፐር ሽቦ መስመሮች የስልክ ገመድ እንዲሰራ የሚያደርጉትን በቂ ኤልክትሪክ ስለሚሸከሙ ለአስተማማኝነቱ የተለመደውን የአገልግሎት መስመር ጋር ሊጣበቁ ይችላሉ። ስለዚህ "የድሮ የተለመዱ" ስልኮች የመጠባበቂያ ባትሪ ሳያስፈልጋቸው የኃይል ማስተላለፊያን ምክንያት በማድረግ በመስራት ይቀጥላሉ። በሌላ በኩል፣ ፋይበርን-መሰረት ያደረገ መሰረተ ልማት የኤሌክትሪክ ኃይልን አይሸከሙም። ይህም ማለት፣ በፋይበር ኔትዎርክ ላይ ያሉት የስልክ ሥርዓቶቹ ሁልጊዜ የቤት ኤሌክትሪክ ላይ ወይም የመጠባበቂያ ባትሪ (BBU) ጋር መያያዝ አለባቸው።

OPC ከኮፐር-ወደ ፋይበር ሽቦ ሽግግር ማድረጉን በንቃት እየቀጠለበት ይገኛል፤ ይህም በቅርቡ ከ Verizon ጋር ድርጅቱ ተመሳሳይ ዋጋን ስለማስቀጠል ያለው ቁርጠኝነት እና በአሁኑ ጊዜ በኮፐር አገልግሎት ስለሚሰጠው የተጠቃሚን ጥበቃዎችን በተመለከተ የተደረጉ ውይይቶች ያካትታል።

በዚያም "ፋይበር እየመጣ ነው" በሚለው ድኅረገጽ ላይ፣ Verizon በሽግግር እና በዝርጋታ ሂደት ወቅት የሚሆነውን እንዲህ ገልጾታል፦

> "የሙብራት ኃይል ፍሰትን በተመለከተ ለእርስዎ የድምጽ አገልግሎት የሚሰጠውን ኃይል እንዲያገኙ ያለምንም ክፍያ የመጠባበቂያ የባትሪ መሳሪያን እንሰጥዎታል፤ ይህም የስልክ ጥሪ ለመቀበል እና ለመደወል፣ ወደ 911 ን አካቶ፣ በእርስዎ የስልክ ሽቦዎች እንዲያደርጉ ያስችሎታል።"

እነዚህ BBU የ D-ሴል ባትሪዎችን ማለትም አስፈላጊ ከሆነ ተጠቃሚዎች በራሳቸው ሊለውጧቸው የሚችሉትን ይይዛል።

የእርስዎን አከባቢ የስልክ አገልግሎትን ለማስቀጠል በተመለከተ ምንም ዓይነት ጥያቄዎች ካልዎት የደንበኛ ቅሬታ ሰሚ ባለሙያዎቻችን ጋር ይደውሉ። OPC ሊረዳ ይችላል!

**ወደ 202.727.3071 ግንኙነት ያድርጉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ info@opc-dc.gov**
**ዌብሳይ: opc-dc.gov**